# የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር አትላንታ

# መተዳደሪያ ደንብ(ረቂቅ)

**ጥር 2019**

BYLAW OF

ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION

IN ATLANTA (Draft)

**January, ....2019**

# የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ /BY LAW

እ አ አ መጋቢት 30 ቀን 2018 ዓ/ም  የፀደቀው፡ መተዳደሪያ፡ ደንብ፡ አንቀጽ  32 ቁጥር 1 እና ቁጥር  2 ለቦርድ በሰጠው ስልጣን መሰረት የተሻሻለ ደንብ።

አንቀጽ  1:  መግቢያ

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ እ አ አ 1983  ኢ.ኢ.አ የተመሠረተ ማህበር ነው።

በአትላንታና አካባቢው  የምንኖር ኢትዮጵያውያን ወይም ኢትዮ አሜሪካውያንን የኮሚኒቲ ማህበሩን በአዲስ መልክ በማደራጀት እና በማጠናከር፤

ሀ-  ማንኛውንም አይነት ችግር በጋራ ለመቋቋም

ለ-  ባህላችንን ታሪካችንንና ቅርጻችንን ጠብቀንና አስተዋውቀን ለትውልድ ለማስተላልፍ

ሐ- የምንኖርበትን አገር ህግና ስርአት አክብረን ማህበራዊ ኑሮአችንን በማስማማትና በማቀናጀት ተጠቃሚ መሆን ለመቻል

መ-   የዘር፤የጾታ፤የሃይማኖት፤የፖለቲካ ወገንተኝነት የሌለበት ወይም የማይካሄድበት

ሠ-  ጠንካራና ለሁላችንም አለኝታ የሚሆን የኮሚኒቲ ማህበር እንዲኖረን ማህበራችን የደረሰበትን እድገት የሚመጥን ደንብ

በማስፈለጉ የበፊቱ መተዳደርያ ደንብ ተሻሽሎ በዚህ ደንብ ተተክትዋል።

ምእራፍ አንድ

## አመሰራረት-Establishment

አንቀጽ 2 : ስያሜ

የማሕበሩ መጠሪያ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ(Ethiopia Community Association in Atlanta, INC or (ECAA) ተብሎ ይጠራል።

# አንቀጽ 3:- የደንቡ ተፈጻሚነት

ይህ ደንብ በአትላንታና አካባቢው  እንዲሁም  በመላው የጆርጂያ ግዛት በሚኖሩ የማህበሩ አባላት ላይ ተፋጻሚ  ይሆናል።

# አንቀጽ 4  : አድራሻ

የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት በአትላንታና አካባቢው  ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ በጆርጂያ ግዛት ልዩ ልዩ ቦታ ቅርንጫፍ መክፈት ይችላል።

# አንቀጽ 5  :ትርጉዋሜ

በሌላ አኳኃን ካልተገለፀ በስተቀር በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ

5.1 ኢትዮ-አሜሪካዊ ማለት በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው በዜግነት አሜሪካዊ የሆኑ የማህበር አባል ማለት ነው።

5.2 አትላንታና አካባቢው ማለት በአትላንታ ከተማ ውስጥ ወይም በሌሎች የጆርጂያ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ የማህበር አባላት ማለት ነው።

5.3 አባል ማለት የማህበሩ አባል የአባላት መመዘኛን ያሙዋሉ ግዴታዎችን የሚወጡ እንዲሁም ተመርጠው በኃላፊነት የሚያገለግሉትን ማለት ነው።

5.4 ቤተሰብ ማለት የትዳር አጋር ልጆች ወይም ወላጆች አንድ ላይ የሚኖሩ ማለት ነው።

5.5 ኢ ኮ ማ አ/ ECAA ማለት የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ ማለት ነው።

5.6 ጠቅላላ ጉባኤ ማለት የማህበሩ የበላይ አካል ሲሆን ሃላፊነታቸዉንና ግዴታቸዉን የፈጸሙ የማህበሩ ጠቅላላ አባላት ማለት ነው። ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩ የመጨረሻ ወሳኝ አካል ነው።

5.7 ቦርድ ማለት በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ  ሰባት አባላት እንዲሁም ከኃይማኖት ተቋዋምና ከልዩ ልዩ ማህበር ወይም ድርጅት የሚወከሉ ግለሰቦች ኮሚኒቲውን በኃላፊነት የሚያገለግል አካል ነው።

5.8 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማለት:-

አምስት አባላት ያሉት በቦርድ የሚመደብ ወይም የሚቀጠር የማህበሩን የእለት ከእለት ሥራ የሚያከናውን ማለት ነው። የቦርድ አባል በሥራ አስፈጻሚ ተመድቦ መሰራት ይችላል።

# ምእራፍ ሁለት

## ዓላማ (Objectives) ፨

## አንቀጽ 6

## ማህበሩ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል።

1. በአትላንታና አካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮ-አሜሪካዊያንን በማቀራረብ የጋራ ባህላቸውንና ታሪካቸውን እንዲያዳብሩ ምቹ የጋራ መድረክ መፍጠር።

2. የኃይማኖት፤ የፆታ፤ የጎሳ፤ የፖሎቲካ ልዩነት ሳይደረግ ማንኛውም አካል እንደ ማህበረሰብ በጋራ መብቱን ለማስከበር ይችል ዘንድ ድርጅታዊ ኃይል መፍጠር።

3. በሞት፤ በህመም፤ በአደጋ፤በአካል ጉዳት **ወይም** በስራ-ማጣት የኢኮኖሚ ችግር ሲ ያጋጥማቸው ለአባላት ድጋፍና እርዳታ ማድረግ።

4. አባሎችና ቤተሰቦቻቸው ለትምህርት፤ለስልጠና፤ ለስፖርት መሰሪያና ለሁሉም አገልግሎት የሚጠሙ በት የኮሚኒቲ ማእከል መገንባት ወይም መግዛት።

5. አባላትና ቤተሰቦቻቸው ከአጉል ባህል፤ከወንጀል፤ከመጥፎ ሱስ፤እንዲርቁ የምክር የስልጠናና መልሶ መቋቋሚያ (Rehabilitation) ድጋፍና እርዳታ መስጠት።

6. ወደ አትላንታና አካባቢው አዲስ ለሚመጡ የማህበረሰባችን አባሎች ከአሜሪካ ባህልና የአኑዋዋር ዘይቤ ጋር የሚተዋወቁበትን የምክር አገልግሎትና ድጋፍ መስጠት።

7 -በአትላንታና አካባቢው የሚኖሩ የማህበረሰባችን አባሎች ላይ የሰብአዊ መብትና የፍትህ መጉዋደል ሲከሰት ችግሩን በህግ አግባብ መቋቋምና ለመከላከል ተገቢውን ትብብር ማድረግ።

8- የማህበረሰባችን አባሎች በሚኖሩበት አካባቢ የፖለቲካ የኢኮኖሚ የባህል የማህበራዊ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት፡ እንዲሁም እንደየዝንቢያላቸው የሙያና የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት ማመቻቸትና ማገዝ።

9 -ወጣቶች የሙያ ስልጠናና የነጻ ትምህርት እድል እና ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እገዛና ድጋፍ መስጠት።

## አንቀጽ 7 የገቢ ምንጭ

ማህበሩ አላማውን ለማሳካት የሚጠቀምባቸው የገቢ ምንጭ፤

1. ከማህበሩ አባላት የሚከፈል የመመዝገቢያና አመታዊ የአባልነት ክፍያ

2. የተለያዩ ዝግጅቶችን ተግባራዊ በማድረግ ከሚገኝ ገቢ

3. የፕሮጀክትሃሳቦች በማመንጨት( በመንደፍ) መንግስታዊና ለጋሽ ለሆኑ ድርጅቶች በማቅረብ ከሚገኝ የገንዘብ ድጎማ:-

4. ከበጎ አድራጊ ግለሰቦችና የማህበሩ አባላት የሚገኝ ድጋፍ ናቸው፡፤

# አንቀጽ 8 የአባላት የገንዘብ ክፍያ

1- **የማህበሩን ደንብ ተቀብሎ አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሆነ ሰው የአባልነት መመዝገቢያና አመታዊ የአባልነት ክፍያ ይከፍላል።**

2. የአባልነት መመዝገቢያንና አመታዊ የአባልነት ክፍያን መጠን የኮሚኒቲ ማህበሩ ቦርድ ይወስናል።

3. በጡረታ ላይ የሚገኙ ሰዎች ለመመዝገቢያና ለአመታዊ ክፍያ የሚከፈለውን ገንዘብ ግማሽ (50%) ብቻ ይከፍላሉ።

# ምእራፍ (ሶስት)

# አወቃቀር (Organizational structure)

## አንቀጽ 9 ጠቅላላ ጉባኤ

ጠቅላላ ጉባኤ ማለት የኮሚኒቲውን አላማ ለማሳካት የአባልነት ግዴታቸውን የተወጡ አባላትን በሙሉ ያካተተ ስብስብ ሲሆን የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል።

1. በማህበሩ ደንብ ላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች እና ክንዋኔ ይመረምራል፤በማንኛውንም የማህበሩ ጉዳይ የበላይ አካልሆኖ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

2. ሰባት የቦርድ አባላትና ሶስት የቁጥጥር ኮሚቴ አባላትን በአስመራጭ ኮሚቴ አቅራቢነት ይመርጣል። የአገልግሎት ጊዜ የጨረሱ ወይም ከአገልግሎት ለመሰናበት የጠየቁ እና ቦርዱ ከአገልግሎት እንዲሰናበቱ የወሰነባቸውን የቦርድ አባላት፤ የቦርድ ተመራጭ ወይም ተወካይ፤ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላትንና የኮሚኒቲውን የእድር ኃላፊዎች ያሰናብታል።

3. በአመት አንድ ጊዜ በመሰብሰብ ከቦርድ ከስራ አስፈጻሚ ከኦዲተር እና ከእድር የቀረበውን የሥራ አፈጻጸም ና የፋይናንስ ሪፓርት ያዳምጣል፤መመሪያና ውሳኔ ይሰጣል፤ አጠቃላይ ሪፖርቱን ያፀድቃል። የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ በቦርድ ከቀረበ ተወያይቶ ያፅድቃል።

4. የቦርዱ ሊቀመንበር አስቸኳዋይ ጠቅላላ ጉባኤ ከጠራ ይሰበሰባል።

5. የተጉዋደሉ የሥራ ምስኮች ካሉ በቦታው በምርጫ ይተካል።

6. አመታዊ በጀት ያጸድቃል፤አፈጻጸሙ ህግና ደንብን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል።

7. ከማህበሩ አባላት መካከል ከግማሹ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልአተ- ጉባኤ ይሆናል።

8. በተጠራው ጉባኤ ከግማሽ በላይ አባላት ካልተገኙ የማህበሩ አባላት አስር መቶኛ (10%) ከተገኙ እና ከእነሱ ሶስት አራተኛው (¾ኛው) ስብሰባው እንዲቀጥል ከተስማሙ ጉባኤው ይካሄዳል።

## አንቀጽ 10 ቦርድ

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ ቦርድ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ ሰባት ሰዎችን ከልዩ ልዩ ተቋማት ወይም ቤተ እምነቶች ወይም ማህበራት ወይም ድርጅቶች ተወክለው በሚላኩ ሰዎች በጥምረት የሚቋቋም የበላይ አካል ነው።

# ተግባር ና ሃላፊነቱ

1. የኮሚኒቲ ማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ ደንቡን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል::

2. የኮሚኒቲው እድር በእድሩ ደንብ መሠረት መመራትና መተዳደሩን ያረጋግጣል።

3. የማህበሩ ንብረትና ገንዘብ በአግባቡ መያዙንና ማንኛውንም ወጪ ለታሰበለት አላማ መዋሉን ይከታተላል፤ መመሪያ ይሰጣል።

4. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚያደርጋቸው የውጭ ግንኙነት ከማህበሩ አላማ ጋር የማይጻረር መሆኑን ይቆጣጠራል ፤ይከታተላል፤መመሪያ ይሰጣል።

5. በስራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም በእድር ኃላፊዎች የሚቀርብ ማንኛውም እቅድ በጀትና የፕሮጀክት ሃሳቦች መርምሮ ያጸድቃል፤ ያሻሽላል፤ይሽራል።

6. በየሶስት ወር በመሰብሰብ ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ከእድር ኃላፊዎች የሚቀርብለትን የማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያዳምጣል፤መመሪያ ይሰጣል፤ያጸድቃል ፤ ያስተካክላል።

7. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እርዳታ (እገዛ) ከጠየቀ የቦርድ አባላት አመታዊ ክፍያ ከአባላት በመሰብሰብ ለዋናው ገንዘብ ያዥ ያስረክባል።

8. የቦርድ አባላት ማህበሩ የሚጠናከርበትንና አባላት ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ዘዴ በማጥናት እና በመከታተል ለቦርድ ያቀርባሉ።

9. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ሊቀጥር የክፍያ መጠን ይወስናል ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኛ ይቀጥራል ደመወዝን ይወስናል። ሠራተኛ ይቀጥራል ደመወዝን ይወስናል። ሠራተኛን እንዳስፈላጊነቱ ያሰናብታል።

10. ማንኛውንም የነጻ አገልግሎትም ሆነ በክፍያ የሚሠራ የኮሚኒቲውን ሠራተኛ፤ወይም የእድር ኃላፊ ከሥራ አመራር ቦርድ ማገድ ወይም ማሰናበት ይችላል።

11. ይህንን ደንብ በማይጻረር መልኩ ቦርድ የራሱን የውስጥ መመሪያ ያዘጋጃል።

12. ተወክለው የሚላኩ የቦርድ አባላት የኮሚኒቲው ድ/ቤት በሚያዘጋጀው ፎርም ላይ ከሚወከላቸው ተቋም አስፈርመው ማቅረብ አለባቸው።

13. ከ$3000.00 (ሶስት ሺህ ዶላር) የሚጠይቅ ወጪ ያጸድቃል።

14. ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፤ ተግባርና ኃላፊነታቸውንም በውስጥ መመሪያ ያጸድቃል።

15- በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ያልተካተተ ወይም ግልጽ ያልሆነ ነገር ሲያጋጥም ቦርድ ተነጋግሮ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ውሳኔ መስጠት ይችላል።

# አንቀጽ 11 የቦርድ ሊቀመንበር

የቦርድ ሊቀመንበር ተወክለውና በጉባኤ ተመርጠው በተሰበሰቡት የቦርድ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለቦርድ ይሆናል።

## ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት

1. የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበርን የቦርድ ስብሰባ ይጠራል፤ በሊቀመንበርነት ይመራል።
2. -የጠቅላላ ጉባኤ መደበኛና አስቸክዋይ ስብሰባ ይጠራል ፤ስብሰባዉንም በሊቀመንበርነት ይመራል።
3. -የቦርድ አባላት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የእድር ኃላፍዎች በህገ ደንቡ መሰረት ተግባራችውን ማከናወናችውን ያረጋግጣል።
4. -የቦርድ አባላት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትና የእድር ኃላፊዎች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃትና በትጋት እንዲወጡ ይከታተላል
5. -ማንኛውንም የሥራ እንቅስቃሴ ለመደገፍ የቦርዱ አባላትን በተለየዩ ኮሚቴ ውስጥ ይመድባል።

## አንቀጽ 12 የቦርድ ም/ሊቀመንበር

1. ሊቀመንበሩ በሌለበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።
2. በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
3. ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሊቀ-መንበር ይሆናል።

## አንቀጽ 13 የቦርድ ፀሃፊ

1. በሊቀመንበሩ በሚሰጠዉ መመሪያ መሠረት የቦርድ አባላትን ስብሰባና የጠቅላላ ጉባኤን የስብሰባ ጥሪ ያደርጋል።
2. የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል
3. በማንኛውም የቦርድ ስብሰባ ወቅት ያለፈውን ቃለ ጉባኤ በማንበብ በነበሩ አባላት ፊርማ ያስፀድቃል።
4. የቦርዱን የድ/ቤት ተግባራት ያከናውናል፤ መዛግብትንና መረጃዎችን ይይዛል፤ ያደራጃል።
5. የማህበሩን አባላት ዝርዝር ይይዛል።
6. ወጭ ደብዳቤዎችን ያዘጋጃል በሊቀመንበሩ ወይም በምክትሉ ተፈርሞ ወደሚመለከተው ያስተላልፋል ገቢ ደብዳቤዎችን እየተከታተላል
7. የቦርድ ድ/ቤትን የሚመለከቱ ሥራወችን ያከናዉናል
8. ተጠሪነቱ ለቦርድ ሊቀመንበር ይሆናል።
9. የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት ተሰባኞች የቦርድ አባላት በኃላፊነታቸው ሥር የሚገኝ የገንዘብ ፤ንብረት፤የሰነድና

ሌሎችንም ቁሳቁሶች ለአዲሶች አባላት ማስረከባቸውን ይቆጥጠራል፤ይመራል፤ያፈራርማል።

አንቀጽ 14 የኦዲት ቁጥጥር ኮሚቴ

**የኢዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ**

**የኢዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ ሶስት የሂሳብ የንብረትና አስተዳደር ሙያተኞች ያሉት አካል ነው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ፡**

**1-የማህበሩን የገንዘብ የሂሳብና የንብረት አያያዝ ደንብ በማዘጋጀት በቦርድ ሊፀድቅ ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ያስተላልፋል።**

**2-የማህበሩንና በማህበሩ ሥር የሚገኙ ማናቸውንም የገንዘብ ዝውውር ወጭና ገቢ ሂሣብ አያያዝ በደንቡ መሠረት መከናወኑን ይቆጥጠራል በየስድስት ወሩ ወይም በቦርድ በተጠየቀ ማናቸውም ጊዜ ሪፖርት ያቀርባል።**

**3-በአመት አንድ ጊዜ ለቦርዱ እና ለጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባል።**

**4-እንዳስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ የገንዘብ ወይም የሥራ አፈጻጸም ምርመራና ኦዲት በማድረግ ለቦርድና ወይም ለጠቅላላ ጉባኤ ያሳውቃል።**

**5-የኮሚኒቲ ማህበሩ ተመራጬች ወይም ተወካዮች የሥራ ዘመን ከመጠናቀቁ ከሁለት ወር በፊት ዝርዝር የኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል። የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት አዲስ የቦርድ አባሎች ነባሮች ወይም ተሰናባቾች እንዲፈራረሙ ያደርጋል።**

**6-የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሁሉም የሥራ ክፍሎች በተግባር ላይ መዋሉም እቅድ ፕሮጀችት በተያዘላቸው በጀትና የጊዜ ገደብ መከናወናቸውን ያረጋግጣል።**

7-የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል።

## አንቀጽ 15 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቦርድ ይመረጣል በጉባኤ የተመረጡት ሰባት የቦርድ አባላትና ተወክለው የመጡት አባሎች የመጀመሪያ ስብሰባ የቦርዱን ሊቀመንበር ም/ሊቀመንበርና ፀሃፊ ከመረጡ በኍላ አምስት የሥራ አስፈጻሚ አባሎችን ይመርጣል።

አምስት የሥራ አስፈጻሚ አባሎች የሥርና ሃላፊነት እንድ ችሎ ታ ሊቀ መንበር ፀሃፊ በሂሳብ ሹም ገንዘብ ያዥ ህዝብ ግኑኙነት የሥራ ዝርዝሮች

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነት፡

1-የማህበሩን የእለት ከእለት የሥራ እንቅስቃሴ ያከናውናል

2-የአባላትን ዝርዝር መረጃ ይይዛል፣ አባላትን ይመዘግባል

3-ማህበሩን የሚያጠናክር እቅድ ይነድፋል በቦርድ የፀደቀውን በተግባር ያውላል

4-በየሶስት ወር የሥራ እንቅስቃሴ ወይም ክንውን ሪፖርት በጹሁፍ ያዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል

5-የማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል ግዴታቸውንም እንዲወጡ ክትትል ያደርጋል

6-የማህበሩን አመታዊ ባጀትና የሥራ እቅድ በማዘጋጀት ለቦርድ ያድቀርብል ሲፀድቅ በሥራ ላይ ያውላል

7-የማህበሩን አላማ ለመተግበር የገቢ ምንጭ ማስገኛ ዘዴዎችን በመንደፍ በቦርድ ሲፀድቅ በተግባር ያዉላል

8-እንዳስፈላጊነቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴ ውይም ግብረ ሃይል በማቁቁም የአጭርና የረጅም ሥራዎችን ማሠራት ይችላል። ኮሚቴ በቦርድ መፅደቅ አለበት።

9-የማህበሩን ገንዘብ ንብረት መረጃ ወይም ሰነድ በጥንቃቄ መያዛቸውን ይከታተላል ያረጋግጣል።

10-በወር አንድ ጊዜ የሥራ አስፈጻሚ ስብስባ ያደርጋል የስራ እንቅስቃሴ ይገመገማል መመሪያ ይሰጣል እንዳስፈላጊነቱና አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል

11-ከሶስት ሺህ $3000.00በላይ ወጭ የሚጠይቅ ማንኛውንም ክፍያ በቦርድ ማጽደቅ አለበት

12-የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብስባ የሚጠራውና የሚመራው በዳሪክተሩ ሲሆን ስብሰባው መካሄድ የሚችለው ሶስት ሰዎች ከተገኙ ነው

13-ከቦርድ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል

አንቀጽ 16 ዳሬክተር

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ዳሬክተር በምርጫ ወይም በቅጥር በቦርድ ይመደባል ተጠሪነቱ ለቦርድ ነው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን በሃላፊነት ይመራል

ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነት

1-የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን የስራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል

2-የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል

3-በቦርድ አባላት ስብሰባ ይሳተፋል

4-የማህበሩ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል የተዝረከረከ አሠራርና ብክነት ሲታይ አስቸኲዋይ የእርማት እርምጃ ይወሰዳል

5-ከሂሳብ ሹሙ ጋር ይክፍያ ሰነድና(form) ቼክ ይፈርማል

6-የኮሚቴውን አባላት የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ በሚመለከት የውስጥ መመሪያ ያዘጋጃል የኮሚቴ አባላት 3/4ኛ ሲስማሙና በሶርድ ሲፀድቅ ተግባር ላይ ያውላል::

7-በቦርድ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል::

አንቀጽ 17 ዋና ጸሃፊ

ዋና ፀሃፊው በምርጫ ወይም በቅጥር በቦርድ ይመደባል ተጠሪነቱ ለዳሪክተር ይሆናል

ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነት

1- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን ጽ/ቤት ያስተዳድራል ያደራጃል ይመራል

2-ወጪና ገቢ ደብዳቤዎችን ይቀበላል ለሚመለከትው የሥራ ክፍሎች ያስራጫል በቅድመ ተከተል ፋይል ያደርጋል

3-የማህበር አባላትን ዝርዝር መረጃ በሚገባ ይይዛል ይጠብቃል

4-የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ እንዲተራ ዳሬክተሩ ሲፈቅድ ስብሰባ ይጠራል የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ ይይሃል በቅድመ ተከተል መረጃውን ፋይል ያደርጋል

5-የማህበሩ ጽ/ቤት ለአባላት ክፍት እንዲሆን እቅድ በማውጣት በኮሚቴው ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል አፈጻፀሙን ይከታተላል፡፤

6-ለ ጽ/ቤት የሥራ አገልግሎት የሚያስፈልጉ እቃዎች ዝርዝር በማውጣት ባጀት ይጠይቃል።

7-የልዩ ልዩ ኮሚቴ ወይም ናኡስ ኮሚቴ የፕሮጀክት እቅዶች በተወሰነላቸው የጊዜ ገደብና አጀት መከናወናቸውን በመከታተል ለዳሬክተሩ ሪፖርት ያቀርባል፡፤

8-ሌሎች በዳሬክተሩ የሚሰጡ መሰል ተግባሪች ያከናውናል

አንቀጽ 18 የህዝብ ግኑኙነት ሃላፊ

የህዝብ ግኑኝነት ሃላፊ በቦርድ የሚመረጥ ቀይም የሚመደብ ወይም ይሚቀጠር ሲሆን ይማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በመገናኛ ብዙሃን በሬዲዮ በቴሌቪዥን  በመጽሄት በበራሪ ጽሁፍ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ መረጃዎችን ይሚያቀናብርና የሚያሰራጭ ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳሬክተሩ ነው።

ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ

1-የማህበሩን አላማና የስራ እንቅስቃሴ በመገናኛ ብዙህን ለህዝብ ያሰራጫል

2-የማህበሩ ዌብ ሳይት ያስተዳድራል ወቅታዊ መረጃዎችን ያስቀምጣል

3-የጠቅላላ ጉባኤውን የቦርድና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውንና የተለያዩ የኮሚቴ ስብሰባዎችን ወይም ዝግጅቶችን በቪዲዮ በመቅረጽ ፋይል ያደርጋል፡፤

**4-አስፈላጊ የሆኑ የሥራም ሆነ የዝግጅት ወይም የስብሰባ ዝግጅቶች በቪዲዮ በመቅረጽ ለህዝብ እንዲተላለፉ ወይም እንዲታዩ ያደርጋል**

**5-የኮሚኒቲውን እንቅስቃሴ ለአባላት ለማሳወቅ መጽሄት ያዘጋጃል ያሰራጫል**

**6-ለሥራው እንቅልቃሴ የሚያስፈልጉትን የእቃዎች** ዝርዝር እና ባጀት ያቀርባል ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል።
7-በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ወይ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን ሃላፊዎች ቃል-መጠየቅ በማድረግ መረጃዎችን አቀነባብሮ ያቀርባል።
8-ኮሚኒቲውን በፈቃደኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉትን በመመልመል ወይም በማዘጋጀት ያቀርባል ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል።
9-መገናኛ ብዙሃንን በሃላፊነት የሚመለከት ኦዲቶሪያል ቦርድ ይሆናል።
10-ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል

አንቀጽ 19 ገንዘብ ያዥ ተግባርና ሃላፊነት
የኮሚኒቲ ማህበሩ ገንዘብ ያዥ በቦርድ የሚመረጥ ወይም የሚመደብ ይሆናል ተጠሪነቱ ለዳሪክተሩ ነው።

1-የኮሚኒቲ ማህበሩን ገቢና ወጭ በዘመናዊ የገንዘብ አያያዝ ዘዴ ይይሃል
2-የማህበሩ አባላት የመመዝገቢያና አመታዊ ክፍያ እንዲፈጸሙ ይከታተላል ማንኛውንም ገቢ በ24ሰዓት ውስጥ ባንክ ያስገባል።
3-ማንኛውንም የገንዘብ ወጭ ከመፈረሙ በፊት የወጭ ማዘዣ ሰነድ በዳሬክተር ወይም በቦርድ የተፈቀደ እና የተፈረመ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።
4-ማንኛውም ወደ ማህበሩ ይሚላክ ወይም የገባ ገንዘብ በማህበሩ ይክክለኛ ደረሰኝ ተመዝግቦ ለላኪው ወይም ለከፋዩ እንዲደርሰው ያደርጋል ደረሰኙም የማህበሩ አርማ ያለበትና የቁጥር ቅደም ተከተል የያዘ መሆኑን ያረጋግጣል ።
5-ሌሎች በዳሬክተሩ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

አንቀድ 20 የሂሳብ ሹም
የኮሚኒቲ ማህበሩ የሂሳብ ሹም በቦርድ የሚመረጥ ወይም የሚመደብ ወይም የሚቀጠር ይሆናል።

የሂሳብ ተግባርና ሃላፊነት

1-ተጠሪነቱ ለዳሬክተሩ ይሆናል።
2-የማህበሩ የገንዘብ አያያዝ ገቢና ወጭ በዘመናዊ መልክ መሆኑን ይቆጣጠራል ያስተካክላል።
3-የገብቢና ወጭ የኮሚኒቲውን የእድሩን ዝርዝር ሪፖርት ለሥራ አስፈጻሚና ለቦርድ በየወሩ ያቀርባል አመታዊ ጉባኤ ሲደረግ የአመቱን ሪፖርት ያቀርባል።
4-የገንዘብ ገቢ አና ወጭ ሰነዶች ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ ደንብ የተከተሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
6-የገቢ ማሰባሰቢያ እቅድ ከሌሎች የሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያዘጋጃል ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያውላል።
7-በየሶስት ወር የሚዘጋጀውን የፋይናንስ ሪፖርት በማህበሩ ውብ ሳይት ላይ እንዲወጣ ያደርጋል፡፤
8-የፌደራል እና የእስቴት ታክስ ወይም የሚከፈል ግብርና እዳ መሠራቱንና መከፈሉን ያረጋግጣል።
9-ሌሎች ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 21
ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም።

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ቦርድ በይም ሥራ አስፈጻሚ ወይም እድር ማንኛውንም ሥራ በጊዜአዊነት ይሁን በቋሚነት ለማሠራት
ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ማቋቋም ይችላሉ።
የኮሚቴው ተጠሪነትና ዝርዝር ተግባር
1-ለማንኛውም ተግባር የሚቋቋም ኮሚቴ ግብረ ሃይል ወይም ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ላቋቋመው አካል ይሆናል።
3-የህግና የማህበራዊ ጉዳይ የጤናና የስፖርት ኮሚቴ የትምህርትና የስልጠና ኮሚቴ የሴቶችና የህጻናት ኮሚቴ የወጣቶች ጊዳይ ኮሚቴ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ ኮሚቴ ችሎታና ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በመጋበዝ በቦርድ ይቋቋማል።
4-ቦርድ ማንኛውንም ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ወይም ግብረ ሃይል አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው ማፍረስ ይችላል።

## አንቀጽ 22
### አባልነት (MEMBERSHIP)
### የአባልነት መመዘኛ
የማህበሩ አባል ለመሆን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሙዋላት ይኖርባቸዋል።

1-እድሜ ከአስራ ስምንት አመት በላይ መሆን አለበት።
2-ኢትዮጵያዊ ወይም እትዮ-አሜሪካዊ መሆን አለበት።
3-የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ተረድተው የተቀበሉና የአባልነት ማመልከቻ የሞላ/ች መሆን አለበት።
4-የመመዝገቢያ ክፍያና አመታዊ ክፍያ መክፈል።

## አንቀአ 23
### የአባላት መብት

1-መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማህበሩን አገልግሎቶች ተጠቃሚ የመሆን ይችላል
2-በስብሰባ ላይ ያለምንም ገድብ ሃሳብን መግለጽ ይችላል
3-የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት አላቸው
4-በህመም፡ በአደጋ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ችግር ምክኒያት አመታዊ ክፍያ መክፈል ባይችሉ ከአባልነት አይሰረዙም

## አንቅጽ 24
### የአባልነት ግዴታዎች

1-በስብሰባ ላይ መገኘት አለባቸው
2-የመተዳደሪያ ደንቦችን ማክበር
3-አመታዊ መዋጮን በወቅቱ መክፈል

## አንቀጽ 25
### ከአባልነት የሚያስወግዱ ድርጊቶች

1-አንድ አባል በአንቀጽ 24 ላይ የተዘረዘሩትን የአባልነት ግዴታዎች ካልፈጸመ ጉዳዩ በቅሬታ ኮሚቴ ታይቶ በቦርድ ሲወሰን ከአባልነት ይሰረዛል
2-ማንኛውም አባል ከአባልነት ከተሰረዘ ምክንያቱ ተዘርዝሮ የጽሁፍ ደብዳቤ ይደርሰዋል።
3-በአባልነት ጊዜ የከፈለው ገንዘብ አይመለስም።

አንቀጽ 26
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
የማህበሩ ቦርድ አሰራርና ስልጣን፣፤
1-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ቦርድ የሚመሰረተው በጠቅላላ ጉባኤ በሚመረጡ ሰባት አባላትና ከልዩ ልዩ የሃይማኖት ተቁማት ከማህበራት ከተለያዩ ድርጅትና ከእዶች ተወክለው የሚመጡ ግለሰቦች በሚደረጉት ስብሰባ ነው፣፤
2-የመጀመሪያው ስብሰባ የቦርዱ ሊቀመንበር ም/ሊቀመንበር ጸሃፊ ከመረጡ በኃላ ከውስጣቸው አምስት አባላትን መምረጥ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመሰርታሉ።
3-የማህበሩ ቦርድ ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤው ሲሆን ሥራ አስፈጻሚው ተጠሪነቱ ለቦርድ ይሆናል
4-ማንኛውም የሃይማኖት ተቋሞ ማህበር ድርጅት ወይም እድር ተወካይ ለመላክ በህግ የተመዘገበና የተረጋገጠ መሆን አለበት።
5-አንቀጽ 26 ቁጥር 4 እንደተጠበቀ ሆኖ ከ25 እስከ 50 አባላት በላይ ተወካይ መላክ ይችላል።
6-በአዲስ መልክ በአባልነት ለመኻፈል የሚፈልኙ ማመልኸጫውኘ ለቦርድ አቅ፟ርበው ወኪል ለመላክ ስድስት ወር መጠበቅ አለባቸው።

አንቀጽ 27
የአገልግሎት ዘመን

1-በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር የማንኛውም የሥራ ክፍል በቦርድ ሥራ አስፈጻሚ ኦዲትና ቁጥጥር የአገልግሎት ዘመን ሁለት(2)አመት ነው።
2-በንኡሱ አንቀጽ የተገለጸው የአገልግሎት ዘመን በድጋሚ ከማንኛውም ተቁም በውክልና የሚመጡ
3- በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጡት አባላት ሁለት ተርም ወይም የመጀመሪያውን ሁለት አመት ጨርሰው በድጋሚ ከተመረጡ ማገልገል ይችላሉ፣፤
4-አራት አመት ያገለገሉ አባላት ከሁለት አመት በኃላ እንደገና ማገልገል ይችላሉ።

አንቀጽ 28
አስመራጭ ኮሚቴ
1-አምስት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ቦርድ ይቁቁማል፣፤
2-አስመርጭ ኮሚቴ የራሱን ሊቀመንበርና ጸሃፊ ይመርጣል።
3-አስመርጭ ኮሚቴ የመገናኛ ብዙሃንና ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለአባሎች የምርጫውን መልክት ያስተላልፋል።
4-አስመራጭ ኮሚቴው ለምርጫው የሚጠቆሙ አባሎችን የሚቀበለው ከኮሚኒቲው

አባሎች ብቻ ነው።
5-አስመራጭ ኮሚቴ የሚያስመርጣቸው ለቦርድ ሰባት አባላት ለእድር አምስት አባላት ለኦዲትና ቁጥጥር ሶስት አባላት ናቸው።
6-አስመራጭ ኮሚቴ የጨወችን ዝርዝርና ፍላጎት የምርጫ ቀንና ቦታውን ቀደም ብሎ ያሳውቃል፥፤
7-የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በምርጫ ውድድር ውስጥ አይገቡም።
8-በምርጫው ቀን ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ምርጫው በግልጽ ይካሄዳል የምርጫው ውጤት በዕለቱ ለጉባኤው ይገልጻል፥፤
9-አስመራጭ ኮሚቴው በፊርማ ያጸደቀውን የምርጫ ሰነድ ለቦርዱ ወይም ለኦዲትና ቁጥጥር በእለቱ ያስረክባል።
10-አዲስ ለተመረጡት ሃላፊዎች በኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አማካይነት ርክክብ ሲደረግ አስመራጭ ኮሚቴ በታዛቢነት መገኘት ይችላል።

አንቀጽ 29
መገናኛ ብዙሃን

1-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ከአባሎችና ከህዝብ ጋር በሚገናኝበት አቅሙ በሚፈቅድለት በክፍያ ወይም በነጻ በሚገኝ መገናኛ ብዙሃን መሠረት መጠቀም ይቻላል፥፤
2-የማንኛውም የአየር የኤሌክትሮኒክስ የህትመት የማህበራዊ ሚዲያ ሶስት አባሎች ባሉት የኢዲቶሪያል ቦርድ ሃላፊነት ይመራል።
3-ለማህበረሰቡ የሚጠቅም ባህል ታሪክ ማህበራዊ ኑሮ ጤና ኢኮኖሚ ትምህርት እና ልዩ ልዩ ጠቃሚ መሊክቶች በባለሙያ ወይም በበጎ ፈቃድኞች እንዲቀርብ ይደረጋል፥፤
4-በኢትዮጵያ የሚፈጸም ወቅታዊ ጉዳዮችን ማንኛውንም መልካም ነገር ወይም መጥፎ ነገር በመረጃ መልክ ይቀርብል።
5-ማንኛውንም ይደስታ፤ የሃዘን፤ ወይም የተቃውሞ ድጋፍ ይሰጣል።

አንቀጽ 30
የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር እድር

1-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር እድር የተቋቋመው በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ሲሆን አገልግሎት የሚሰጠው በእድር አባልነት ለተመዘገቡ የኮሚኒቲው አባላት ብቻ ነው።
2-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር እድር የራሱ የሥራ ደንብ እና በእድሩ ደንብ የጸደቀውን ገንዘብ መክፈል ነው።
3-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር እድር ተግባርና አገልግሎቱ በተመዘገቡና ግዴታቸውን በትክክል ለሚፈጽሙ አባላት ወይም የአባል ቤተሰብ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ በእድሩ ደንብ የጸደቀውን ገንዘብ መክፈል ነው።

4-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ የእድሩን አጠቃላይ የሂሳብ አሰራር ገቢና ወጭ እንዲሁም የሥራ ሂደት ይቆጣጠራል።

5-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ እድር ተጠሪነቱ ለቦርድ ነው።

6-የእድሩ ሃላፊዎች ሚንም አይነት ገንዘብ ቦርድ ሳይፈቅድ ማዘዋወር አይችልም።

7-የድር ገንዘብ ወጭ የሚሆነው የእድር አባል ወይም ቤተሰብ ላይ የሞት አደጋ ሲደርስ ብቻ ነው

8-የሚከፈለው የገንዘብ መጠን በድሩ ደንብ ተደንግጉውል።

9-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ እድር ማንኛውንም ሰነድ በኮሚኒቲው ጽ/ቤት ይቀመጣል።

10-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ቦርድ የእድሩ የበላይ ወሳኝ አካል ሲሆን ጥፋት ከተገኘ የእድሩን ሃላፊ አንዱን ወይም ሁለቱን ከስራ ማገድ ወይም ማሰናበት ይቻላል።

11-የእድር ድንብ በቦርድ ሊሻሻል ይችላል።

12-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ቦርድ የእድሩን አጠቃላይ አሠራር ይከታተላል ይቆጣጠራል።

13-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር እድር በምንም አይነት መንገድ እራሱን ከኮሚኒቲ ማህበሩ ማውጣት ወይም መለየት አይችልም።

14-የእድር አመራር መርጫን ቦርዱ በሃላፊነት ያስፈጽማል።

15-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የእድር አባላትን ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል።

16-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር እድር ኮሚቴ ከኮሚኒቲው ተለይቶ ጽ/ቤት መያዝ ወይም መከራየት አይችልም።

17-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር እድር አመራር ቦርድ ሳያውቅ ሳያጸድቅ ምንም አይነት ውሳኔ መወሰን አይችልም።

18-በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ህገ-ደንብና በእድሩ የሥራ ደንብ መካከል ቅራኔ ቢፈጠር የኮሚኒቲ ማህበሩ ደንብ ገዥ ይሆናል።

አንቀጽ 31
መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

1-ይህ መተዳደሪያ ደንብ እንዳስፈላጊነቱ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል።

2-ይህ የመተዳደርያ ደንብ እንዳስፈላጊነቱ በከፊል ወይም በሙሉ በ 2/3ኛ የቦርድ አባላት ድምጽ ለውጥ ሊሻሻል ወይም ሊጸድቅ ይችላል።

3-የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ቦርድ በ 2/3ኛ ድምጽ ደንቡን መለወጥ ወይም ማጽደቅ ካልቻለ ደንቡ ለጉባኤ ቀርቦ በድምጽ ብልጫ ይጸድቃል።

አንቀጽ 32
ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

**1-ይህ ደንብ ከ--ቀን--ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።**
**2-ይህ ደንብ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ከዚህ በፊት ይሰራበት የነበረው ደንብ ተሰርል በዚህ ደንብ ተተክቶዋል**